# የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ የግል ድርጅቶች

# ሀብት የሚከበርበት፣የሚያዝበት እና ዕዳ

# የሚሰበሰብበት አፈጻጸም መመሪያ

## ቁጥር 05/2016

የግ.ድ.ሠ.ማ.ዋ.አ

ታህሳስ 2016 ዓ.ም

## መመሪያ ቁጥር 05/2016

## የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ የግል ድርጅቶች ሀብት የሚከበርበት፣ የሚያዝበትን እና ዕዳ የሚሰበሰብበትን አፈጻጸም መመሪያ

የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ የግል ድርጅቶች ሀብት የሚከበርበት፣ የሚያዝበት እና የሚፈለግባቸው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ፣ ወለድ እና ቅጣት የሚሰበሰብበት የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአሠራር ሥርዓቱ የግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮን በወቅቱ እንዲከፍሉ የሚያደርግና የተሰበሰበው ገንዘብ በኢንቨስትመንት ላይ ውሎ የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር የሚያስችል በመሆኑ፤

የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1268/2014 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 13 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ የግል ድርጅቶች ሀብት የሚከበርበት፣የሚያዝበት እና ዕዳ የሚሰበሰብበት አፈጻጸም መመሪያ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ የግል ድርጅቶች ሀብት የሚከበርበት፣የሚያዝበት እና ዕዳ የሚሰበሰብበት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 05/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፣

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1. "አዋጅ" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1268/2014 ነው።

2.2. "የጡረታ መዋጮ"ማለት በአዋጁ አንቀጽ 10 መሰረት ከግል ድርጅቱና ከግል ድርጅት ሠራተኛ በየወሩ እየተሰበሰበ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የሚደረግ መዋጮ ነው።

2.3. "የጡረታ መዋጮ ዕዳ"ማለት በአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የሚደረግ የጡረታ መዋጮ ሲሆን፣ ወለድ እና ቅጣትን ይጨምራል።

2.4. "የጡረታ መዋጮ ከፋይ"ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 3 ንዑስ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ የሚሸፈን ድርጅት ወይም ተቋም ነው፡፡

2.5. "የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢ አካላት" ማለት የጡረታ መዋጮ ገቢ እንዲሰበስቡ በአዋጁ አንቀጽ 11 ላይ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ሲሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት በአስተዳደሩ ውክልና የሚሰጣቸውን አካላት እና አስተዳሩንም ይጨምራል፡፡

2.6. "ሀብት" ማለት ሊያዙ እና ሊከበሩ ከማይችሉ ሀብቶች በስተቀር የጡረታ መዋጮ ከፋዩ በሊዝ የያዘውን መሬት ጨምሮ ማናቸውም ቤት ወይም ህንጻ ሥራ የሚከናወንበት ድርጅት፣ ልዩ ልዩ ዕቃዎች፣ በሌላ ሰው ዘንድ ያለው ወይም በሌላ ሰው ዘንድ የሚገኝ ወይም የሚከፈለው ገንዘብ፣ ቼኮች፣ የሚተላለፉ ሰነዶች፣ ቦንዶች ወይም ለገንዘብ የተሰጡ ሌሎች ዋስትናዎች፣ በኩባንያ ውስጥ ያለው የአክሲዮን ድርሻ፣ በጋራ በተያዘ ሀብቶች ላይ ያለው ድርሻ ወይም ማናቸውም ሊሸጡ የሚችሉ ሌሎች ሀብቶች ናቸው፡፡

2.7. "ሀብት ማስከበር" ማለት አስተዳደሩ የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ሀብት ወይም ንብረት ከመያዙ በፊት ባለበት እንዲቆይና እንዳይንቀሳቀስ የሚወሰደው እርምጃ ነው፡፡

2.8. "መያዝ" ማለት በማናቸውም መንገድ የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ሀብት መያዝ ሲሆን፣ የጡረታ መዋጮ ከፋዩ የሆነን ገንዘብ/ሀብት በእጁ ከሚገኝ ሰው ለጡረታ መወጮ ገቢ ዕዳ እንዲውል መሰብሰብንም ይጨምራል፡፡

2.9. "ማገድ" ማለት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ የሚፈለግበት የግል ድርጅት ሀብት እና ንብረት እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ለሦስተኛ ወገን የስም ዝውውር እንዳይደረግ ክልከላ ማድረግ እና ማስከበር ነው፡፡

2.10. "መውረስ" ማለት ለውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ክፍያ ተይዞ በግልጽ ጨረታ ሊሸጥ ያልቻለን የግል ድርጅት ሀብት እና ንብረት ባለቤትነት ወይም ባለንብረትነት በህግ የማግኘት ሥርዓት ነው፡፡

2.11. "የታክስ ወኪል" ማለት በፌዴራል ወይም በክልል የታክስ አስተዳደር ህግ መሰረት በገቢ ሰብሳቢው አካል የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

2.12. "የበላይ ኃላፊ"ማለት የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የበላይ ኃላፊ ወይም ተወካዩ ነው፡፡

2.13. "ኃላፊ" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ የመሰብሰብ ሥልጣን የተሰጠው የሥራ ክፍል ኃላፊ ነው፡፡

2.14. "አስተዳደር"ማለት የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ነው፡፡

2.15. በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

2.16. በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል፡፡

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ያለባቸው የግል ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. ለጡረታ መዋጮ ዕዳ አሰባሰብ ሀብት የሚያዝበት መንገድ

4.1. የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ የግል ድርጅቶች የሚፈለግባቸው የጡረታ መዋጮ በሚከተለው አኳኋን ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

ሀ) የጡረታ መዋጮ ባለ ዕዳውን የሚንቀሳቀስ ሀብት በመያዝ እና በመሸጥ፤

ለ) የጡረታ መዋጮ ባለዕዳውን የማይንቀሳቀስ ወይም ልዩ ተንቀሳቃሽ ሀብት በማስከበር፣ በመያዝ እና በመሸጥ፤

ሐ) የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታውን ያልተወጣ የግል ድርጅት ሀብት በእጁ የሚገኝ ወይም የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው የያዘውን ሀብት ለጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል እንዲያስረክብ በማድረግ፡፡

4.2. የጡረታ መዋጮ ባለዕዳውን የመደበኛ ሥራ ሀብት ጨምሮ ማናቸውም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሀብት እስኪሸጥ ድረስ የማስተዳደር ተግባር የሚከናወነው በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው ወይም እርሱ በሚመድበው ተረካቢ አካል ይሆናል፡፡

5. ለጡረታ መዋጮ ዕዳ አሰባሰብ ንብረት የሚያዝበትና የሚሸጥበት ሥርዓት

በውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት የሚያዝ ሀብት ለማስከበር፣ለመያዝ እና ግልጽ ጨረታ አውጥቶ ሽያጭ ለማካሄድ እንደ አግባቡ የሚከተሉት ተግባራት መከናወን አለባቸው፡-

5.1. ሀብት የመያዝ፣ የማስከበር እንዲሁም ድርጅት የማሸግ ተግባር ለመፈጸም ድጋፍ የሚሰጡ የፖሊስ አካላትና የአካባቢው የቀበሌ ወይም የወረዳ አስተዳደር ተወካዮች እንዲገኙ ማድረግ፤

5.2. የተያዘ ወይም እንዲከበር የተደረገ ተንቀሳቃሽ ሀብት ለሀብቱ ማቆያ ወይም ማከማቻ ወደ ተዘጋጀ ቦታ እንዲጓጓዝ ማድረግ እና የድርጅቱ ሥራ የሚካሄድበትን ጨምሮ ማናቸውም የጡረታ መዋጮ ባለዕዳ የማይንቀሳቀስ ሀብት ባለበት ተከብሮ እንዲቆይ ወይም እንዲታሸግና ጥበቃ እንዲደረግለት ማድረግ፤

5.3. በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት የሚያዝ ሀብት ማቆያ/ማከማቻ/ የሚውል ቦታ ማዘጋጀት እና ንብረቱ ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኝ ከመንግሥታዊ እና ሌሎች አካላት ድጋፍ ጠይቆ ማግኘት፤

5.4. በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ሀብትን ግምት እንዲያወጡ ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው አካላት የጨረታ መነሻ ዋጋ ግምት እንዲወጣ ማድረግ ፤

5.5. በግልጽ ጨረታ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች በጨረታ የሚሸጠውን ሀብት በቦታው ተገኝተው ማየት እንዲችሉ ሀብቱ የሚገኝበት ቦታ በሥራ ሰዓት ለተመልካቾች ክፍት እንዲሆን ማድረግ፤

5.6. በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት የተያዘን ሀብት ለመሸጥ የሚሰራጨውን የግልጽ ጨረታ ሽያጭ ሰነድ ማዘጋጀት እና ማጽደቅ፤

5.7. በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ሀብት እንደአግባቡ በአንድ ጊዜ ወይም በቅደም ተከተል በግልጽ ጨረታ እንዲሸጥ ማድረግ፤

5.8. በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ሀብት አስፈላጊው ሆኖ ሲገኝ በግልጽ ጨረታ አማክሎ የሚሸጥበትን ዘዴ መወሰን፤

5.9. የተያዘው/የተከበረው ሀብት የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ ወይም በኩባንያ ውስጥ ያለ ድርሻ ወይም በውርስ የተገኘ ሀብት የሆነ እንደሆን ሽያጩን ለማካሄድ ሦስተኛ ወገን መጠቀም፤

5.10. በግልጽ ጨረታ የተሸጠ ሀብት ዋጋ ሙሉ በሙሉ መክፈሉን በማረጋገጥ የሀብቱ ባለቤትነት በገዥው ስም እንዲዛወር ለሚመለከተው የመንግስት አካል ማስታወቅ፤

5.11. በዚህ መመሪያ መሰረት ከሁለተኛ ጊዜ ግልጽ ጨረታ በኋላ ያልተሸጠን ሀብት በመነሻ ግምቱ ዋጋ መረከብ ወይም መውረስ እና በድርድር መሸጥ፤

5.12. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢ አካላት ሠራተኞች ወይም ከጡረታ መዋጮ ከፋዩ ጋር ዝምድና ወይም ግንኙነት ያላቸው ሰዎች የጡረታ መዋጮ ባለዕዳውን ሀብት ለመግዛት በግልጽ ጨረታ እንዳይሳተፉ ማድረግ፤

5.13. በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት ከሀብት መያዝ፣ ማስከበርና መሸጥ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የጡረታ መዋጮ ባለዕዳን ሀብት ስለመያዝ</u>

### 6. ሀብት ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ

6.1. ሀብትን ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ የሀብት መያዝ እርምጃ ከመወሰዱ ከ30 ቀናት አስቀድሞ ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ መስጠት ወይም መድረስ አለበት፡፡

6.2. ሃብት ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ በዋናነት የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ መሆን አለበት፡፡

ሀ) በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢ አካላት ቀደም ሲል ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ የተላከውን የጡረታ መዋጮ ዕዳ ማስታወቂያ የደብዳቤ ቀን እና ቁጥር፤

ለ) ከጡረታ መዋጮ ከፋዩ የሚፈለገውን ያልተከፈለ የጡረታ መዋጮ ዕዳ የገንዘብ መጠን፤

ሐ) አስቀድሞ የተከፈለ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ካለ ተቀናሽ የተደረገ መሆኑን፤ እና

መ) ማስታወቂያው እስከተጻፈበት ቀን ድረስ በቀሪነት የሚፈለግበት አጠቃላይ የጡረታ መዋጮ ዕዳ፡፡

6.3. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢ አካላት የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ሀብት በመሸጥ ከሽያጭ የሚገኘውን ገንዘብ የጡረታ መዋጮ ዕዳውን ብቻ ሳይሆን ሀብቱን ከመያዝ፣ ከማጓጓዝ፣ ከማስተዳደር፣ከማስገመት እና ከመሸጥ ጋር በቀጥታ ለተያያዙ የአፈጻጸም ተግባሮች ማከናወኛ ለሚወጣ ወጪ መሸፈኛ የሚያውለው መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ መጻፍ ይኖርበታል፡፡

7. ሀብትን ስለመያዝ ማስታወቂያ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

7.1. ሀብትን ስለመያዝ የሚሰጠው ማስታወቂያ ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ በሚከተለው አኳኋን እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ በሚሆንበት ጊዜ፡-

ሀ) ድርጅት ከሆነ በድርጅቱ የንግድ ሥራ ቦታ ለሚገኘው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ለታክስ ወኪሉ በአካል በመስጠት፤

ለ) ግለሰብ ከሆነ በቀጥታ ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ ወይም ለታክስ ወኪሉ በአካል በመስጠት፡፡

የጡረታ መዋጮ ከፋዩ የኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ፣

ሀ) በኢትዮጵያ ወኪል የሆነው ድርጅት ሥራ ቦታ ለሚገኘው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ወኪል በአካል በመስጠት፤

ለ) ግለሰብ ከሆነ ለታክስ ወኪሉ በመስጠት፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽ መሰረት ማስታወቂያውን የሚቀበለው ወይም የሚረከበው ሰው በማስታወቂያው ቅጂ ላይ የተቀበለ ለመሆኑ ማረጋገጫ እንዲሆን ስሙንና የተረከበበትን ቀን በመጻፍ ሊፈርም ይገባል፡፡

7.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7.1 መሰረት ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ ማስታወቂያውን መስጠት ካልተቻለ በጡረታ መዋጮ ከፋዮ ወይም በወኪሉ ሥራ ማከናወኛ ቦታ ወይም መኖሪያ ቤት አመችና በግልጽ በሚታይ ስፍራ ሦስት እማኞችን በማስፈረም ወይም የፖሊስ አባል በተገኘበት እንዲለጠፍ ይደረጋል፡፡

7.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7.1 እና 7.2 መሰረት ለጡረታ መዋጮ ከፋይ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ማስታወቂያ ማድረስ ካልተቻለ ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ የሆነ ግለሰብ ወይም ድርጅት ከሆነ የጡረታ መዋጮ ከፋዩ በተመዘገበበት የድርጅቱ ወይም የግለሰብ አድራሻ በመላክ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

7.4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7.2 እና 7.3 መሰረት ማስታወቂያዎችን ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ ማድረስ ካልተቻለ እንደ አስፈላጊነቱ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ኢሜልና ፋክስን ጨምሮ ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ በማስተላለፍ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

7.5. በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ዘዴዎች በመጠቀም ማስታወቂያ ማድረስ ካልተቻለ የፍርድ ቤት ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ጋዜጣ ማስታወቂያውን በማውጣት ለጡረታ መዋጮ ከፋይ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

7.6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7.5 መሰረት የፍርድ ቤት ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ጋዜጣ የሀብት መያዣ ትዕዛዝ የወጣበት የጡረታ መዋጮ ከፋይ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ማስታወቂያው እንደደረሰው ይቆጠራል፡፡

8. ሀብት ከመያዙ በፊት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

8.1. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢ አካላት የጡረታ መዋጮ ዕዳ ማስታወቂያ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሰረት ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የጡረታ መዋጮ ባለዕዳውን ሀብትና የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት መረጃ ከሚመለከተው የመንግሥት አካላት ጋር በመሆን ማሰባሰብ አለበት፡፡

8.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8.1 መሰረት የሚሰበሰበው መረጃ የጡረታ መዋጮ ባለዕዳውን ሀብት ዓይነት፣ ብዛት፣ የሚገኝበትን አድራሻ፣ የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ሀብት በማን ይዞታ ሥር እንደሚገኝ፣ በዋስትና የተመዘገበ መሆን አለመሆኑን፣የፍርድ ቤት እግድ ያለበት መሆን አለመሆኑን እና የመሳሰሉ መረጃዎችን የሚጨምር መሆን አለበት፡፡

8.3. በተሰበሰበው መረጃ ወይም በተገኘ ጥቆማ መሰረት የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የሚመለከተው የበላይ ኃላፊ የጡረታ መዋጮ አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ እንደሆነ እና የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ለመክፈል ፈቃደኛ አለመሆኑ ከታወቀ የ30 ቀናት የጊዜ ገደብ ወይም በማስጠንቀቂያ የተሰጠውን ቀነ ገደብ ሳይጠብቅ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ሀብቱን በመያዝ የጡረታ መዋጮ የመሰብሰቡ አፈጻጸም እንዲካሄድ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

8.4. ሀብቱን የመያዝ ትዕዛዝ ለጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ወይም ለጡረታ መዋጮ ባለዕዳው የታክስ ወኪል፣የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ሀብት በእጁ ወይም በይዞታው ለሚገኝ ለማንኛውም ሰው፣ ሀብቱን ወይም መብቱን ወይም ድርሻውን ለሚመዘግብ አግባብ ላለው ሰው ወይም ፍርድ ለሚያስፈጽም አካል መሰጠት አለበት፡፡

9. ሀብትን ስለማስከበር

9.1. መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ ማስጠንቀቂያውን ለመላክ ሲወስን ወዲያውኑ የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ሀብት በዋስትናነት እንደተሰጠ ሀብት ሳይሸጥ፣ ሳይለወጥ፣ ሳይከፈል፣ በባለሀብትነትም ሆነ ባለይዞታ ሳይዛወር ተከብሮ እንዲቆይ እንዲደረግ ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ፣ ሀብት ለሚመዘግብ አግባብ ላለው የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት ወይም የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ሀብት በእጁ ለሚገኝ ሰው ማስታወቂያ ይልካል፡፡

9.2. ሀብት ተከብሮ እንዲቆይ የሚሰጥ የማስታወቂያ ይዘት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ 2 የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ መሆን አለበት፡፡

9.3. ሀብት የሚመዘግበው አካል በጡረታ መዋጮ ከፋዩ ስም የተመዘገበ ሀብት ተከብሮ እንዲቆይ ማድረግና የተከበረውን ሀብት ዓይነት ለጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ማስታወቅ አለበት፡፡

9.4. የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ሀብት በእጁ የሚገኝ ማናቸውም ሰው ሀብት የማስከበሩ ማስታወቂያ ባይደርሰው ኖሮ ሀብቱን ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ የሚያስረክብ መሆኑን እና ሀብቱ በእጁ ወይም በይዞታው እንዲቆይ መደረጉ ወጪ ያስከተለበት መሆኑን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ያቀረበ እንደሆነ የዚህ ዓይነቱ ወጪ ተሰልቶ ከሀብቱ ሽያጭ ከተገኘ ገቢ ላይ እንዲከፈለው ይደረጋል፡፡

10. ስለማይከበሩና ስለማይያዙ ሀብቶች

10.1. ከዚህ በታች የተመለከቱት ሀብቶች በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት የማይከበሩና የማይያዙ ናቸው፡፡

ሀ) ለጡረታ መዋጮ ባለዕዳውና ለቤተሰቡ የዕለት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ልብሶች፣ ለምግብ ማብሰያ አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶች፣ አልጋ ፣የአልጋ ልብስ፣ ፍራሽ፣ ትራስ እና ብርድ ልብስ፤

ለ) ለሙያ ሥራ አስፈላጊ የሆነ የእጅ መሳሪያዎች፤

ሐ) የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው በግብርና ሥራ የሚተዳደር ከሆነ በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል አስተያየት ለሥራው አገልግሎት በቂ ሆነው የሚገመቱ የቀንድ ከብቶች፣ የጋማ ከብቶች፣ የዘር እህልና ፍጹም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች፤

መ) ለጡረታ መዋጮ ባለዕዳውና ለቤተሰቡ ለ3 ወራት መተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ ወይም ቀለብ፤

ሠ) የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው የሚያገኘው የጡረታ ገንዘብ፣ ባል/ሚስት ለሚስቱ/ለባልዋ ከፍቺ በኃላ ለልጆች ቀለብ የሚከፍሉት ገንዘብ፤

ረ) የባልና ሚስት የቃል ኪዳን ቀለበት፣ ሜዳሊያ/ኒሻን፤

ሰ) የጠበቆች፣ የሀኪሞች እና የአካውንታንቶች/ኦዲተሮች ፋይሎችና ሰነዶች፤

ሸ) እንዳይከበር፣እንዳይሸጥ እና ለዕዳ መክፈያ እንዳይሆን በማናቸውም ሌላ ህግ ወይም በፍርድ ቤት የተወሰነ ማናቸውም ዓይነት ሀብት፣

10.2. መያዝ፣ መሸጥና ማዘዋወር በህግ ክልከላ የተደረገባቸው ዕቃዎች፣ ለመያዝ፣ለመጠቀም ወይም ለመሸጥ ልዮ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች፣ በህግ መሰረት የሚወረሱ ወይም ኮንትሮባንድ፣ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ዕቃዎች ከተገኙ አግባብ ያለውን አካል በማሳወቅ እንዲረከቡ ማድረግ ወይም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ አለበት፡፡

10.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10.1 (ለ)(ሐ) እና (መ) አፈጻጸም የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የማይከበር ሀብትን መጠን ሊወሰን ይችላል፡፡

11. ሀብት ስለመያዝ

11.1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሰረት ማስጠንቀቂያ የተሰጠው የጡረታ መዋጮ ከፋይ ማስጠንቀቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የጡረታ መዋጮ ዕዳውን ያልከፈለ እንደሆነ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 10 ከመያዝ ነጻ ከተደረጉት ወይም በፍ/ቤት አስቀድሞ ከተከበረ ወይም በዋስትና ከተያዘ ሀብት በስተቀር ማናቸውንም የጡረታ መዋጮ ባለዕዳውን ሀብት የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ይይዛል፣ ለጡረታ መዋጮ ዕዳው ክፍያ እንዲውል ያደርጋል፡፡

11.2. በፍ/ቤት አስቀድሞ የተከበረ ወይም በዋስትና የተያዘ ሀብት ላይ ገቢ ሰብሳቢው አካል የቀዳሚነት መብት አቤቱታ ያቀርባል፤

11.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11.1 የተደነገገው ቢኖርም የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የጡረታ መዋጮ ከፋዩ የጡረታ መዋጮ አሰባሰቡን የሚያደናቅፍ፣ ሀብት የማሸሽ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ተግባር በመፈጸም ላይ ያለ መሆኑን ሲረዳ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ክፍያ ማስታወቂያ ከተላከ በኃላ መቆየት ያለበትን የ30 ቀናት ጊዜ ገደብ ሳይጠብቅ በአፋጣኝ ሀብቱን የመያዝ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

11.4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11.1 እና 11.2 የሚያዘው ሀብት በተቻለ መጠን ከጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ከሚፈለገው የጡረታ መዋጮ ዕዳ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡

11.5. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ሀብት ከመያዙ በፊት ሀብቱ እንዲያዝ የተሰጠውን የውሳኔ/የትዕዛዝ ቅጂ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ለተገለጹት አካላት መስጠት አለበት፡፡

11.6. ከእርሻ ሰብል በስተቀር፣

ሀ) ማናቸውም የሚንቀሳቀስ ሀብት የሚያዘው በጡረታ መዋጮ ባለዕዳው እጅ የሚገኘውን ሀብት በመረከብ ነው፡፡

ለ) የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ወይም ወኪሉ በተገኘበት የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ሀብቱን ቆጥሮና መዝግቦ ይረከባል፣ በቦታው የተገኙት ሁሉ የተቆጠረውን ሀብት በፊርማቸው ያረጋግጣሉ፣ የተቆጠረው ሀብት ዝርዝር ቅጂ ለጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ይሰጣል፡፡

ሐ) የተያዘው ሀብት የከበሩ ማዕድናት ማለትም አልማዝ፣ እንቁ፣ ወርቅና ብር የሆነ እንደሆነ መጠኑ በሚዛን ተመዝኖ እና የጥራት ደረጃው ህጋዊ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመርምሮ ዋጋው በባለሙያ ተገምቶ በዝርዝሩ ላይ መገለጽ አለበት፡፡

11.7. የተያዘው ወይም የተከበረው ሀብት በቀላሉ የሚበላሽ ወይም ዋጋ የሚያጣ/የሚቀንስ የሆነ እንደሆነ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በማናቸውም ዘዴ ወዲያውኑ ሊሸጠው ይችላል፡፡

11.8. የሚያዘው ወይም የሚከበረው ሀብት የእርሻ ሰብል ወይም ፍራፍሬ የሆነ እና በማሳው ላይ ያለ ከሆነ ትዕዛዙን በሥፍራው በመለጠፍ፣ ሰብሉ ታጭዶ የተከመረ ወይም በመወቃት ላይ ያለ ወይም የእንስሳት መኖ ክምር ከሆነ በክምሩ ወይም በአውድማው አቅራቢያ በመለጠፍ ይሆናል፡፡

11.9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11.8 የተከበረው ሀብት ስለሚጠበቅበት ሁኔታ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የሚሰጠው ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ሰብሉን የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ወይም ተወካዩ ባለበት ሊያጭድ ወይም ሊወቃ ይችላል፡፡

11.10. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11.8 አፈጻጸም የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ሰብሉን ካጨደ ወይም ከወቃ በኋላ የተገኘውን የምርት መጠን የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ወኪል ባለበት ተቆጥሮ ሁሉም እንዲፈራረሙ ከተደረገ በኃላ ሀብቱ የሚጠበቅበትንና የሚሸጥበትን ሁኔታ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ይወስናል፡፡

11.11. እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የታዘዘው ሀብት በጡረታ መዋጮ ባለዕዳው እጅ ያልገባ ከሌላ ሰው የሚጠየቅ በሚተላለፍ ሰነድ ያልተደገፈ ገንዘብ ወይም በፍርድ ቤት ክስ በማስፈረድ መብት ያገኘበት ገንዘብ ወይም ሌላ ሀብት በሆነ ጊዜ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ሌላ ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ሀብቱን ወይም ገንዘቡ በእጁ የያዘ ሰው ገንዘቡን ወይም ሀብቱን ለጡረታ መዋጮ ባለዕዳውም ሆነ ለሌላ ማናቸውም ሰው ሳይሰጥ/ሳያስተላልፍ በእጁ እንዲያቆይ በጽሁፍ ማዘዝ ይኖርበታል፡፡

11.12. የሚያዘው ወይም የሚከበረው ሀብት የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ከሌሎች ሰዎች ጋር በተካፋይነት ወይም በጋራ የሚጠቀምበት ወይም የጋራ ባለሀብት የሆነበት ሀብት ወይም በሽርክና የያዘው ሀብት ወይም በውርስ የተገኘ ሀብት ሲሆን የመያዙ ወይም የማስከበሩ ሥርዓት የሚፈጸመው ድርሻውን ለሌላ ሰው አሳልፎ እንዳይሰጥ፣በዋስትና እንዳያሲዝ ወይም በማናቸውም ምክንያት እንዳያስተላልፍ ከሽርክናው የሚገኘውን ትርፍ እንዳይወስድ የማገድ ትዕዛዝ ለጋራ ባለሀብቶቹ ወይም ለሽሪኮች ወይም ድርሻውን ለሚያስተዳድሩ አካላት በመስጠት ነው፡፡

11.13. የሚያዘው ሀብት የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው የሚያገኘው ደመወዝ በሚሆንበት ጊዜ በየወሩ እየተቀነሰ ወይም የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በሚያዘው ሁኔታ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡ የማንኛውም ሠራተኛ ደመወዝ እንዲያዝ የሚሰጠው ትዕዛዝ ከሠራተኛው የሚፈለገውን የጡረታ መዋጮ ዕዳ መጠን እና የሚያዘውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

11.14. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11.13 ድንጋጌ መሰረት ተቀናሽ የሚደረገው የገንዘብ መጠን ለሠራተኛው ከሚከፈለው ደመወዝ የሥራ ግብር እና የጡረታ መዋጮ ተቀናሽ ሆኖ ከሚደርሰው አንድ-ሦስተኛ መብለጥ የለበትም፡፡

11.15. እንዲያዝ የታዘዘው ሀብት የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ የሆነ እንደሆነ እና በፍርድ ቤት ያልተያዘ ከሆነ የማስከበሩ ወይም የማስያዙ ሥርዓት የሚፈጸመው የሚተላለፈው የገንዘብ ሰነድ ተይዞ በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል እንዲቀመጥ በማድረግ ወይም በሌላ አካል የተያዘም ከሆነ ሌላ ትዕዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ እንዳይለቀቅ የሚያግድ ትዕዛዝ በመስጠት ይሆናል፡፡

11.16. እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የታዘዘው ሀብት በፍርድ አስፈጻሚ መ/ቤት ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤት እጅ የሚገኝ ከሆነ ሀብቱ ወይም ሀብቱ የሚያስገኘው ማናቸውም ጥቅም ተጠብቆ እንዲቆይ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ትዕዛዝ በመስጠት ማስከበር ይችላል፡፡

11.17. የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው በውድ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ ስላለው ሀብት መረጃ እንዲሰጥ ተጠይቆ ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ቁልፉን ለመስጠት እምቢተኛ ከሆነ ባንኩ ወይም የገንዘብ ተቋሙ ቁልፉን እንዲሰጥ በማድረግ የባንኩ ተወካይና የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ወይም ወኪሉ እንዲገኙ ማስታወቂያ በመስጠት በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ተከፍቶ ሀብቱ እንዲመዘገብና እንዲታሸግ ይደረጋል፡፡

11.18. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የጡረታ መዋጮ ባለዕዳን የመንግሥት ቦንድ ወይም ከኢንቨስትመንት ወይም ከኢንሹራንስ በየጊዜው የሚከፈል ሂሳብ እንዳይከፈልና ሌላ ትዕዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ተይዞ እንዲቆይ ለሚመለከተው አካል ትዕዛዝ በመስጠት እንዲከበር ማድረግ ይችላል፡፡

11.19. እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የተወሰነው የማይንቀሳቀስ ወይም ልዩ ተንቀሳቃሽ ሀብት ከሆነ የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ሀብቱን ለሌላ ሰው እንዳይሰጥ፣ እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ መብቱን ለማንም ሰው እንዳያዛውር እንዲሁም ሌሎች ሰዎች በሀብቱ ላይ የዋስትና መብትን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት መብት እንዳይኖራቸው የሚያግድ ትዕዛዝ የማይንቀሳቀስ ሀብት ለሚመዘግበው አካል በመስጠት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

11.20. በዚህ አንቀጽ መሰረት የግል ወይም የሙያ ጉዳዮችን ፋይሎች የያዘ ኮምፒውተር በተያዘ ጊዜ ርክክቡ መከተል ስለሚገባው የአፈጻጸም ሥርዓት በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ውሳኔ ይሰጣል፡፡

12. የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ደንበኞች ሀብት ስለመመለስ

የተያዘው ወይም በማሸግ የተከበረው ሀብት የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ደንበኞች ማንኛውም ሀብት በውስጡ የሚገኝበት እንደሆነ ሀብቱ ከተያዘ በኃላ ባሉት 15 የሥራ ቀናት ውስጥ ደንበኞች ማስረጃቸውን እያቀረቡና ያልተከፈለ የአገልግሎት ቀሪ ሂሳብ እየከፈሉ እንዲረከቡ መደረግ አለበት፡፡

13. ልዩ ጥንቃቄ ስለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች

13.1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 በተመለከተው መሰረት ሀብት ሲያዝ ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው ልዩ ልዩ ኬሚካሎች ወይም ንጥረ ነገሮች የሚሸጡባቸው፣ የሚከማቹባቸው ወይም የሚመረቱባቸው ሲሆን እነዚህን ኬሚካሎች ወይም ንጥረ ነገሮች ለመያዝ የሚያስፈልገው ጥንቃቄ በቅድሚያ መታወቅና አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት መደረግ ይኖርበታል፡፡

13.2. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13.1 መሰረት ሀብት ከመያዙ በፊት ወይም እና በኃላ ሊበላሽ የሚችልበት ሁኔታ ካለ ሊወስዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ዝርዝር ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

13.3. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በዚህ አንቀጽ በተመለከተው መሰረት ልዩ ጥንቃቄ የሚሹ ዕቃዎች ስለአያያዙ፣ስለአጠቃቀሙና አሻሻጡ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ትብብር ሊጠይቅ ይችላል፡፡

14. የተያዘ ወይም የተከበረ ሀብት ስለሚለቀቅበት ሁኔታ

14.1. የተያዘ ወይም የተከበረ ሀብት ለሀብቱ መያዝ ወይም መከበር ምክንያት የሆነው የጡረታ መዋጮ ዕዳ በሙሉ የተከፈለ እንደሆነ የተያዘው ሀብት ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ ይለቀቅለታል፡፡

14.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14.1 መሰረት የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ሀብት የተለቀቀ በሚሆንበት ጊዜ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ወጪ ሀብቱን ለሚመዘግብ አካል የመያዝ ወይም የማስከበሩ ትዕዛዝ መነሳቱን መግለጽ አለበት፡፡

15. በተያዘ ወይም በተከበረ ሀብት ላይ የሚቀርብ አቤቱታን ስለመመርመር

15.1. የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው የተያዘው ወይም የተከበረው ሀብት በህግ የማይከበር ወይም የማይያዝ ነው በማለት የሀብቱ ሽያጭ ከመካሄዱ በፊት ለጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል አቤቱታ ሲቀርብለት አቤቱታውን በማጣራት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

15.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 15.1 መሰረት ውሳኔው ሀብቱ መያዝ የለበትም የሚል ከሆነ ሀብቱ እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

15.3. የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው የጡረታ መዋጮ ባለመከፈሉ ምክንያት የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የያዘው ወይም ያስከበረው ሀብት ይገባናል የሚሉ ሦስተኛ ወገኖች የሚያቀርቡትን አቤቱታ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ተቀብሎ ይመረምራል፡፡

15.4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 15.3 መሰረት ሀብቱ አላግባብ የተያዘ መሆኑን እና የአቤቱታ አቅራቢው ሀብት መሆኑን በበቂ ማስረጃ ያረጋገጠ እንደሆነ በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የተያዘው ሀብት እንዲለቀቅ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 16. ስለይግባኝ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት አለው፡፡

## 17. ገንዘብ በተያዘ ጊዜ ደረሰኝ ስለመስጠት

17.1. የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ዕዳውን አጠናቆ ባለመክፈሉ በሚሰጥ የመያዝ ትዕዛዝ መሰረት በጡረታ መዋጮ ባለዕዳው እጅ፣ መኖሪያ ቤት ወይም መደበኛ ሥራውን ከሚያከናውንበት ቤት እንዲሁም ከባንክና ከማናቸውም የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ካለበት ሰው ላይ ገንዘብ የተያዘ እንደሆነ ገቢ ለተደረገው ገንዘብ ደረሰኝ በመስጠት ከጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ላይ ሂሳቡ እንዲቀነስ ይደረጋል፡፡

17.2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 17.1 አፈጻጸም የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የጡረታ መዋጮ ከፋዩን የጡረታ መዋጮ ዕዳ የመክፈል ግዴታ ከተጣለበት ሰው ላይ ገንዘቡን መረከቡን በደብዳቤ ሲገልጽለት የሚገባ ሲሆን ለጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የከፈለውን ገንዘብ እንዲከፍል ክስ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

17.3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ የሚሰጠው ደረሰኝ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ነው፡፡

## 18. ሀብትን በመያዝ ለጡረታ መዋጮ ዕዳ መክፈያ ማዋልን በውክልና ስለማስፈጸም

18.1. የጡረታ መዋጮ ባለዕዳ ሀብት የሚገኘው ከጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ጽ/ቤት አካባቢ ርቆ በሚገኝ ቦታ እንደሆነ የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ሀብት እንዲያዝ የተሰጠውን ውሳኔ ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር በመላክ ሀብቱ በሚገኝበት አካባቢ ባለው የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ቅርንጫፍ አማካይነት በውክልና እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

18.2. ሀብቱ እንዲያዝ የተሰጠው ውሣኔና አስፈላጊ ሰነዶች የደረሰው ተወካይ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ሀብቱን በመያዝና በመሸጥ ገንዘቡን በወከለው አካል በተከፈተው የጡረታ መዋጮ ገቢ መሰብሰቢያ የባንክ ሂሳብ ገቢ በማድረግ ማስረጃውን መላክ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የተያዘውን የጡረታ መዋጮ ባለዕዳውን ሀብት ስለመሸጥ

### 19. ሀብትን ስለመገመት

19.1. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ያስከበረው፣ የያዘው ወይም ታሽጎ እንዲቀመጥ ያደረገውን የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ሀብት ለመሸጥ እንዲችል የሀብት ግምት ሥራ ማከናወን በሚችሉ ግምት አውጪ አካላት እንዲገመት ያደርጋል፡፡

19.2. በዚህ ዓይነት የተገመተው የሀብት ዋጋ የግልጽ ጨረታ መነሻ ዋጋ ሆኖ ይወሰዳል፡፡

### 20. ሀብት ስለሚሸጥበት ዘዴ

20.1. በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የተያዘውን ወይም የተከበረውን ሀብት ዓይነት፣ ያለበትን ቦታ፣ የሀብቱን ሁኔታ እና ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሽያጩ በግልጽ ጨረታ ዘዴ የሚከናወን መሆኑን ይወስናል፡፡

20.2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 20.1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የተያዘው ወይም በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የተረከበው ሀብት የሚበላሽ ዕቃ በሚሆንበት ጊዜ የግልጽ ጨረታ ሂደቱን ሳይከተል ሀብቱ የሚሸጥበትን ሌላ ዘዴ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ይወሰናል፡፡

20.3. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በግልጽ ጨረታ የሚሸጠው የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ሀብት ከአንድ በላይ ከሆነ ቢሸጥ የሽያጩ ዋጋ ዕዳውን ለመሸፈን ይችላል ተብሎ በሚገመተው መጠን ሀብቱ በሙሉ በአንድ ጊዜ ወይም ከፊል ሀብቶቹ በቅድም ተከተል እንዲሸጡ ለማድረግ ይችላል፡፡

20.4. የሀብት ሽያጭ በቅድም ተከተል የሚደረገው የከፊል ሀብቱ ሽያጭ የጡረታ መዋጮ ዕዳውን ለመሸፈን የሚበቃ መሆኑ ወይም ሀብቱን ለመሸጥ ብዙ ጊዜ የማይወሰድ መሆኑ ሲታመን ነው፡፡

20.5. ለውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ አሰባሰብ ሀብት የሚሸጠው ለዕዳ አሰባሰብ በተቋቋመ የሥራ ክፍል በሚቋቋም ኮሚቴ ወይም እንደ አግባቡ ሀብት በመሸጥ ዕዳ እንዲሰበስብ በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በሚቋቋም ኮሚቴ ወይም በተቋቋመ የሥራ ክፍል ነው፡፡

### 21. የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ስለማውጣት

21.1. በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት የተያዘው ሀብት በግልጽ ጨረታ የሚሸጠው የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ እንዲወጣ በማድረግ ነው፡፡

21.2. የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያው የሀብቱን ዓይነት፣ የሀብቱ የግልጽ ጨረታ መነሻ ግምት፣ ሀብቱ የሚገኝበትን ቦታ፣ ግልጽ ጨረታው የሚካሄድበትን ቀንና ሰዓት፣የሀብቱን ባለቤት ስም፣ በግልጽ ጨረታው ተሳታፊዎች በጨረታው ለመካፈል የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተመሰከረለት ቼክ ወይም በሲፒኦ ወይም በጥሬ ገንዘብ እንዲያስይዙ እና የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ግልጽ ጨረታውን የመሰረዝ መብት እንዳለው የሚገልጽ መሆን አለበት።

21.3. የግልጽ ጨረታው ማስታወቂያ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ፎርም ዓይነት መዘጋጀት ይኖርበታል።

21.4. ማናቸውም የሚንቀሳቀስ ሀብት ሽያጭ በግልጽ ጨረታ የሚከናወነው የግልጽ ጨረታው ማስታወቂያ ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ አሥራ አምስት ቀን በኋላ መሆን አለበት።

21.5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 21.4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ወይም ልዩ ተንቀሳቃሽ ሀብት የሆነ እንደሆነ ሽያጩ የሚከናወነው የግልጽ ጨረታው ማስታወቂያ ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን አንስቶ ከ30 ቀናት በኋላ ይሆናል።

21.6. የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣ በኋላ የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ያለበትን ገጽ ፎቶ ኮፒ በማድረግ ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች በመለጠፍ በግልጽ ጨረታው የሚካፈሉት ሰዎች ብዛት እንዲጨምር ጥረት መደረግ አለበት።

21.7. በግልጽ ጨረታ የሚሸጠው ሀብት ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣ ከሆነ በግልጽ ጨረታው የሚሸጠውን ሀብት በራድዮ ወይም በምስል በማስደገፍ ማስታወቂያው በቴሌቭዥን እንዲተላለፍ ሊደረግ ይችላል።

## 22.ግልጽ ጨረታ ስለማካሄድ

22.1. የግልጽ ጨረታ ሥነ-ሥርዓቱ ከመጀመሩ በፊት በግልጽ ጨረታ የሚካፈሉ ሰዎች ስም ዝርዝር ይመዘገባል፣ በግልጽ ጨረታው ተሳታፊዎች በጨረታው ለመካፈል ተገቢውን መያዣ የመነሻ ዋጋውን 10 % በባንክ በተመሰከረለት ቼክ ወይም በሲፒኦ ወይም በጥሬ ገንዘብ እንዲያስይዙ ይደረጋል።

22.2. በመጀመሪያ ግልጽ ጨረታ በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት የተያዘው ሀብት ከግልጽ ጨረታ የመነሻ ዋጋ በታች ሊሸጥ አይችልም።

22.3. የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው ወይም የጋራ ባለሀብቶች በጨረታው ለመሳተፍ አስፈላጊውን መስፈርት ካሟሉ እና በግልጽ ጨረታው ላይ ያቀረቡት ዋጋ ከከፍተኛ የግልጽ ጨረታ ዋጋ ጋር እኩል የሆነ እንደሆነ በአንደኛ ደረጃ የጡረታ መዋጮ ባለዕዳው በሁለተኛ ደረጃ የጋራ ባለሀብቶች በቅድሚያ የመግዛት መብት ይኖራቸዋል፡፡

22.4. በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የተያዙ ሀብቶች የሚሸጡበትን ዝርዝር አካሄድ የሚወስንና የጨረታ ሥርዓቱን የሚመራ የጨረታ ኮሚቴ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ሊያቋቁም ይችላል፡፡

23.የግልጽ ጨረታ አካሔድ ሥነ-ሥርዓት

የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የተያዘውን ሀብት በግልጽ ጨረታ ሲሸጥ ጨረታውን በሚከተለው አኳኋን ያከናወናል፡፡

24.1. የግልጽ ጨረታው ማስታወቂያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 መሰረት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

24.2. የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተነገረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነድ ማቅረብ አለባቸው፡፡

24.3. የግልጽ ጨረታ ሰነድ ለማቅረቢያ በተወሰነው የመጨረሻ ቀን ሀብቱ የተያዘበት የጡረታ መዋጮ ከፋይ ወይም ወኪሉ በተገኘበት ግልጽ ጨረታው ይከፈታል፡፡

24.4. ለግልጽ ጨረታው ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች ከፍተኛ ዋጋ የሰጠው የጨረታው አሸናፊ ይሆናል፡፡

24.5. የግልጽ ጨረታው ውጤት የፀና የሚሆነው የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ የወከለው ሰው የጨረታውን ሪፖርት ሲያፀድቀው ይሆናል፡፡

24 ሁለተኛ ግልጽ ጨረታ ስለማውጣት

24.1. በጡረታ መዋጮ ዕዳ የተያዘው ሀብት በመጀመሪያው ግልጽ ጨረታ ያልተሸጠ እንደሆነ የአንደኛ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ በወጣበት አኳኋን ሁለተኛ የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት እንዲሸጥ ይደረጋል፡፡

24.2. ሁለተኛ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ አፈጻጸም አግባብ ያላቸው የመጀመሪያ የግልጽ ጨረታ ሥነ-ሥርአቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

25. በሁለተኛ ግልጽ ጨረታ ስላልተሸጠ ሀብት

25.1. ሀብቱ በሁለተኛ ግልጽ ጨረታ ያልተሸጠ እንደሆነ የጨረታ ኮሚቴው የጡረታ ፈንዱን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ካመነበት የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በግምቱ እንዲረከበው ወይም ሦስተኛና ከሦስተኛ በላይ ግልጽ ጨረታ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

25.2. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ የወከለው ሰው ጨረታው በተለየ ሁኔታ እንዲፈፀም ካልወሰነ በስተቀር በሁለተኛው ግልጽ ጨረታ ያልተሸጠው ሀብት በሦስተኛ ወይም ከሦስተኛ ጊዜ በላይ በሚካሄድበት ጊዜ የግልጽ ጨረታውን መነሻ ዋጋ በመቀነስ ሀብቱ እንዲሸጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ሦስተኛ ወይም ከሦስተኛ ጊዜ በላይ የሚደረግ ግልጽ ጨረታ ሲካሄድ አግባብ ያላቸው የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ጊዜ የግልጽ ጨረታ ሥነ-ሥርዓቶች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

26. የግልጽ ጨረታ አፈጻጸም ሪፖርት ስለማቅረብ

ጨረታውን እንዲያስፈጽም የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው ያዋቀረው አካል፡-

26.1. ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ቅጽ በተመለከተው መሰረት የግልጽ ጨረታውን አካሄድ የሚያሳይ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

26.2. ሪፖርቱን የግልጽ ጨረታው አስፈፃሚ ከሆነው ኃላፊ አስተያየት ጋር የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ ለወከለው ሰው ለውሳኔ ያቀርባል፡፡

27. ሀብት በግልጽ ጨረታ ከተሸጠ በኋላ ስለሚፈፀም ተግባር

27.1. የተያዘ ሀብት በግልጽ ጨረታ ከተሸጠበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ የጨረታው አሸናፊ ለጨረታው ማስከበሪያ ያስያዘውን ገንዘብ እና የውል ማስከበሪያው 10% በዕለቱ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ለዚሁ ተግባር በከፈተው ልዩ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረጋል፡፡ ሌሎች ተሳታፊዎች ያስያዙት ገንዘብ ተመላሽ ይሆናል፡፡

27.2. የግልጽ ጨረታ አሸናፊ ያስያዘውን ገንዘብ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በዕለቱ ገቢ ለማድረግ በበቂ ምክንያት ያልተቻለ እንደሆነ በዕለቱ ያልከፈለውን ቀሪ ክፍያ ግልጽ ጨረታው ከተካሄደበት ዕለት ጀምሮ በሚቆጠሩ 15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ለጡረታ መዋጮ ገቢ መሰብሰቢያ በከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

27.3. አሸናፊው ተጫራች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 27.2 በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን ገቢ ካላደረገ የ7 ቀን ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለ በጨረታ ወቅት ያስያዘው የውል ማስከበሪያ ገንዘብ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የሚደረግ መሆኑ በጽሑፍ ይገልጽለታል፡፡

27.4. የግልጽ ጨረታው አሸናፊ ማስጠንቀቂያው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ7 ቀን ጊዜ ውስጥ በልዩነት የሚፈለግበትን ሂሳብ ገቢ ካላደረገ ግልጽ ጨረታው ተሰርዞ ያስያዘው ገንዘብ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል፡፡

27.5. የግልጽ ጨረታው አሸናፊ ቀሪውን ሂሳብ ባለመክፈሉ ጨረታው የተሰረዘ እንደሆነ ጨረታው የመጀመሪያ ከሆነ የመጀመሪያ ግልጽ ጨረታ እንዳልተደረገ፣ ሁለተኛ ግልጽ ጨረታ ከሆነ ሁለተኛ ጨረታ እንዳልተደረገ ይቆጠራል፡፡

28. የተሸጠውን ሀብት ለገዥው ስለማስረከብ

28.1. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በግልጽ ጨረታ የተሸጠው ሀብት ዋጋ ሙሉ በሙሉ መከፈሉን ካረጋገጠ ተንቀሳቃሽ ሀብት ከሆነ ለአሸናፊው ወዲያውኑ ያስረክባል፡፡

28.2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 28.1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሸጠው ሀብት የማይንቀሳቀስ ወይም ልዩ ተንቀሳቃሽ ሀብትና የባለቤትነት ስም ለማዘዋወር ምዝገባ የሚያስፈልገው ከሆነ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የሀብት ባለቤትነት መብት በገዥው ስም እንዲዛወር አግባብ ላለው የመንግሥት አካል በጽሑፍ ያስታውቃል፡፡

28.3. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በግልጽ ጨረታ የሸጠውን የጡረታ መዋጮ ባለዕዳ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ሀብት መዝጋቢ አካላት ንብረቶች በገዥው ስም እንዲዛወር የሚሰጠውን ትዕዛዝ ባይፈጽሙ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች አግባብ ባለው ህግ መሰረት በህግ ይጠየቃሉ፡፡

29. በግልጽ ጨረታ ያልተሸጠን ሀብት ስለማስረከብ

29.1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተመለከተው ሊሸጥ ያልቻለ ሀብት የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል እንዲረከበው ውሳኔ የተሰጠ እንደሆነ፣ ይህንኑ ውሳኔ የሀብቱ ባለቤት በጽሑፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

29.2. በዚህ አንቀጽ መሰረት የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የተረከበውን ንብረት ለአስተዳደሩ የማስረከብ ኃላፊነት አለበት፡፡

29.3. አስተዳደሩ በግምቱ የተረከበውን ሀብት እስከሚሸጠው ድረስ ለጡረታ ፈንዱ የተሻለ ጥቅም በሚያስገኝ መንገድ ሊያከራይ ይችላል፡፡

30. የጡረታ መዋጮ ዕዳን ስለማቀናነስ

30.1. በግልጽ ጨረታ የተሸጠ ሀብት ወይም የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የተረከበው ሀብት በተሸጠበት ወይም የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በተረከበበት ዋጋ ልክ የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ከሚፈለግበት ዕዳ እንዲቀነስ በማድረግ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ክፍያ ደረሰኝ ተቆርጦ ለጡረታ መዋጮ ባለዕዳው መስጠት ይኖርበታል፡፡

30.2. በግልጽ ጨረታ ከተሸጠው ሀብት የተገኘ ገንዘብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 30.1 በተመለከተው መሰረት እንዲቀናነስ ከተደረገ በኂላ የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ላይ የሚፈለግ ቀሪ ዕዳ ካለ፣ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ለዕዳው ክፍያ የሚውል የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ሌላ ማናቸውም ሀብት በመያዝ መሸጥ ይችላል፡፡

30.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 30.1 በተመለከተው መሰረት የጡረታ መዋጮ ከፋዩ የሚፈለግበት የጡረታ መዋጮ ዕዳ እና ሌሎች ወጪዎች ከተቀነሱ በኃላ ተራፊ ገንዘብ ካለው ወዲያውኑ ለጡረታ መዋጮ ከፋዩ ይመልስለታል፡፡

31. ስለ ገንዘብ ሰነዶች

31.1. የገንዘብ ሰነዶች፣ቼኮች፣ቦንዶች እና ተመሳሳይ ሰነዶች ለጡረታ መዋጮ ዕዳ ክፍያ እንዲውሉ የሚደረጉት ተወርሰው የመክፈያ ቀናቸው ሲደርስ ወደገንዘብ እንዲለወጡ በማድረግ ነው፡፡

31.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 31.1 ላይ የተመለከከቱትን ሰነዶች ወደ ገንዘብ የመለወጥ ግዴታ ያለበት ማንኛውም አካል ሰነዱን ወደ ገንዘብ ለውጦ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

32. ስለ አበል ክፍያ

ንብረት ለመያዝ ድጋፍ ለሚያደርጉ የፖሊስ እና የቀበሌ አስተዳደር አካላት የሚከፈለው አበል በከፍተኛ አመራሩ ይወሰናል፡፡

33. <u>ተጠያቂነት</u>

የዚህን መመሪያ አሠራር እና አፈጻጸም የጣሰ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

34. <u>ሀብትን የመያዣና የመሸጫ ወጪዎች</u>

የጡረታ መዋጮ ባለዕዳውን ሀብት በመያዝና በመሸጥ ለጡረታ መዋጮ ዕዳ ክፍያ የማዋል ሥርዓት ወጪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የተሽከርካሪ መጎተቻ ወጪ፣
2. የተያዙ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የወጣ ወጪ፣
3. የመጋዘን ወጪ፣
4. የቁልፍ መቁረጫና አዲስ ቁልፍ መግዣ፣
5. የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ወጪ፣
6. ለአጫራቾች የአገልግሎት ክፍያ፣
7. ዋጋ ማስገመቻ፣

8. የጥበቃ ወጪ፤
9. ንብረቱን እንዲያዝ ድጋፍ እንዲያደርጉ ለተወከሉ የፖሊስ አባላት እና የቀበሌ አስተዳደር አካላት የሚከፈል አበል፤
10. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ልዮ ልዮ ወጪዎች፤

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

35. የመተባበር ግዴታ

የሚመለከታቸው አካላት ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሀብት በማስከበር፣በመያዝ በመሸጥ እና የስም ዝውውር በማድረግ ረገድ ከጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

36. መሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የተያዙ ወይም የተከበሩ ሀብቶች በዚህ መመሪያ መሰረት ፍጻሜ ያገኛሉ።

37. መመሪያው በስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በአስተዳደሩ ሥራ አመራር ቦርድ ከጸደቀበት ከጥር 1 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል።

የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር

ተክለወልድ አጥናፉ
የሥራ አመራር ቦርድ
ሰብሳቢ

## የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋትና አስተዳደር

## የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ሀብት ማስከበሪያ ማስታወቂያ

ቀን ______________________

ቀጥር ______________________

የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር ______________

ለ______________________

አድራሻ--------- አዲስ አበባ ---------- ክፍለ ከተማ ____________ ቀበሌ____________

የቤት ቁጥር ______________ የስልክ ቁጥር __________

ክልል __________ ወረዳ/ከተማ__________ ቀበሌ______ የቤ.ቁ__________

ስልክ ቁጥር______________________

| ተ.ቁ | የዕዳው ዓይነት | የጡረታ መዋጮ ያልተከፈለበት ጊዜ | | የገንዘብ መጠን | | የተከፈለ | | በቀሪ የሚፈለግ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከ | እስከ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| 1 | ዋና ገንዘብ | | | | | | | | |
| 2 | ቅጣት | | | | | | | | |
| 3 | ወለድ | | | | | | | | |
| 4 | ድምር | | | | | | | | |

ብር(..................................................................)

ከዚህ በላይ መጠኑ የተገለጸውና ለጡረታ ፈንድ መከፈል ያለበት የጡረታ መዋጮ የሚፈለግብዎ መሆኑን በመግለጽ በቁጥር ______________ በቀን ____________ የተመዘገበው የጡረታ መዋጮ ዕዳ ማስታወቂያ እንዲደርስዎ መደረጉ ይታወቃል፡፡

ሆኖም የጡረታ መዋጮ ዕዳ የመክፈል ግዴታዎች ፈጽመው ባለመገኘትዎ በአዋጅ ቁጥር 1268/2014 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 13 ላይ ለጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ማናቸውም ሀብት በመያዝ ለጡረታ መዋጮ ገቢ አሰባሰብ እንዲያውል በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ከዚህ በታች የተገለፁትን ______________________________________________ ሀብቶች ለሚፈለገው የጡረታ መዋጮ እና ልዩ ልዩ የአፈጻጸም ወጪዎች ለማዋል በዚህ ማስታወቂያ እንዲከበሩ የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

"ከሰላምታ ጋር"

የኃላፊ ፊርማ

- የዕዳው መጠን ዕዳው እስከተሰላበት ጊዜ ብቻ ያለውን ዕዳ የሚያመለክት መሆኑ ይታወቅ፡፡

## የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋትና አስተዳደር
## የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ሀብት ማስከበሪያ ማስታወቂያ

ቀን_______________

ቀጥር _______________

ለ/ የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ንብረት በእጁ ለሚገኝ ወይም

የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ማናቸውም ዓይነት ክፍያ የመፈፀም ግዴታ ስለአለበት/

---------------------------------------------

የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በአዋጅ ቁጥር 1268/2014 አንቀጽ 10 እና 12 መሰረት መክፈል ያለበት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ተሰልቶ ለአቶ/ለወ/ሮ_____________ አድራሻ _________ ክልል_ __________ክ/ከተማ__________ቀበሌ_______ ግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር____________ በቁጥር ____________ በቀን__________ እንዲደርሰው በተደረገው የጡረታ መዋጮ ዕዳ ማስታወቂያ የተገለጸው ቀጥሎ የተመለከተው:-

| ተ.ቁ | የዕዳው ዓይነት | የጡረታ መዋጮ ያልተከፈለበት ጊዜ | | የገንዘብ መጠን | | የተከፈለ | | በቀሪ የሚፈለግ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከ | እስከ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| 1 | ዋና ገንዘብ | | | | | | | | |
| 2 | ቅጣት | | | | | | | | |
| 3 | ወለድ | | | | | | | | |
| 4 | ድምር | | | | | | | | |

በፊደል ብር_______________________________

የጡረታ መዋጮ ዕዳ ክፍያ ጥያቄ የቀረበለት ቢሆንም ግዴታን ለመወጣት ፈቃደኛ ባለመሆን የተጠየቀው የጡረታ መዋጮ ዕዳ ሳይከፈል ይገኛል፡፡

ስለሆነም ይህ ማስታወቂያ ከደረስዎት ቀን ጀምሮ በጡረታ መዋጮ ከፋዩ ስም የተቀመጠ ገንዘብ ወይም ሊከፍሉት የሚገባ ማናቸውም ዓይነት ክፍያ ወይም በእጅዎ/በይዞታዎ/ የሚገኘው የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ሀብት ወይም በሀብቱ ላይ ያለው መብት በአዋጅ ቁጥር 1268/2014 አንቀጽ 12 እና የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ የግል ድርጅቶች ሀብት የሚያዝበትን እና የጡረታ መዋጮ ገቢ የሚሰበሰብበትን አፈጻጸም ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር ---/2016 አንቀጽ __________መሰረት እንዲከበር የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

"ከሰላምታ ጋር"

የኃላፊ ፊርማ

ግልባጭ፣

- የዕዳው መጠን ዕዳው እስከተሰላበት ጊዜ ብቻ ያለውን ዕዳ የሚያመለክት መሆኑ ይታወቅ፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ... ዋና ሥራ አስፈፃሚ ... -01

# የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋትና አስተዳደር
# የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ሀብት ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ

ቀን ____________________

ቁጥር ____________________

የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር ____________

ለ____________________

አድራሻ--------- አዲስ አበባ ---------- ክፍለ ከተማ ____________ ቀበሌ____________

የቤት ቁጥር ____________ የስልክ ቁጥር ____________

ክልል ____________ ወረዳ/ከተማ____________ ቀበሌ________ የቤ.ቁ____________

ስልክ ቁጥር____________________

| ተ.ቁ | የዕዳው ዓይነት | የጡረታ መዋጮ ያልተከፈለበት ጊዜ | | የገንዘብ መጠን | | የተከፈለ | | በቀሪ የሚፈለግ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከ | እስከ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| 1 | ዋና ገንዘብ | | | | | | | | |
| 2 | ቅጣት | | | | | | | | |
| 3 | ወለድ | | | | | | | | |
| 4 | ድምር | | | | | | | | |

በፊደል ብር____________________

ከዚህ በላይ መጠኑ የተገለጸውና የጡረታ መዋጮ ዕዳ ማስታወቂያ በቁጥር ____________ በቀን ________ የተላከልዎ ቢሆንም የጡረታ መዋጮ ዕዳ የመክፈል ግዴታዎን ለመወጣት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡

ስለዚህ ይህ ማስታወቂያ ከደረስዎ ቀን ጀምሮ በ-------------- ቀናት ውስጥ ክፍያ ካልፈጸሙ በአዋጅ ቁጥር 1268/2014 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 13 እና የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ የግል ድርጅቶች ሀብት የሚያዝበትን እና የጡረታ መዋጮ ገቢ የሚሰበሰብበትን አፈጻጸም ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር ---/2016 አንቀጽ ____________መሰረት ማናቸውንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሀብትዎን በመያዝ ለጡረታ መዋጮ ገቢ አሰባሰብ እና ከዚሁ ጋር ለተያያዙ የአፈጻጸም ተግባሮች ማከናወኛ ለሚወጣ ወጪ መሸፈኛ እንዲውል የሚደረግ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

"ከሰላምታ ጋር"

የኃላፊ ፊርማ

- የዕዳው መጠን ዕዳው እስከተሰላበት ጊዜ ብቻ ያለውን ዕዳ የሚያመለክት መሆኑ ይታወቅ፡፡

## የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋትና አስተዳደር
## የጡረታ መዋጮ ከፋዩን ሀብት ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ

ቀን ____________________

ቀጥር ____________________

ለ ____________________

.............................................................

የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በአዋጅ ቁጥር 1268/2014 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ድርጅትዎ የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ ዕዳ ማስታወቂያ ለ -------------------------------- ---------------------- አድራሻ--------- አዲስ አበባ ---------- ክፍለ ከተማ ______________ ቀበሌ_______ ______የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ____________________ በቁጥር ________________በቀን________ ______ እንዲደርሰው በተደረገው ማስታወቂያ የተገለጸው ቀጥሎ የተመለከተው፡-

| ተ.ቁ | የዕዳው ዓይነት | የጡረታ መዋጮ ያልተከፈለበት ጊዜ | | የገንዘብ መጠን | | የተከፈለ | | በቀሪ የሚፈለግ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከ | እስከ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| 1 | ዋና ገንዘብ | | | | | | | | |
| 2 | ቅጣት | | | | | | | | |
| 3 | ወለድ | | | | | | | | |
| 4 | ድምር | | | | | | | | |

በፊደል ብር____________________________________

ከዚህ በላይ መጠኑ የተገለጸውና የጡረታ መዋጮ ዕዳ ማስታወቂያ በቁጥር ________________ በቀን ____________ በተጻፈ ደብዳቤ የተላከልዎ ቢሆንም ድርጅትዎ የጡረታ መዋጮ ዕዳ የመክፈል ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡

ስለዚህ ይህ ማስታወቂያ ከደረስዎ ቀን ጀምሮ በ-------------- ቀናት ውስጥ ክፍያ ካልፈጸሙ በአዋጅ 1268/2014 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 13 እና የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ የግል ድርጅቶች ሀብት የሚያዝበትን እና የጡረታ መዋጮ ገቢ የሚሰበሰብበትን አፈጻጸም ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር ---/2016 አንቀጽ ____________መሰረት በጡረታ መዋጮ ከፋዩ ስም የተቀመጠ ገንዘብ ወይም ሊከፍሉት የሚገባ ማናቸውም ዓይነት ክፍያ ለጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ገቢ እንዲያደርጉ ወይም በእጅዎ/በይዞታዎ የሚገኝ የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ማናቸውም ሀብት ለጡረታ መዋጮ ገቢ አሰባሰብ እና ከዚሁ ጋር ለተያያዙ የአፈጻጸም ተግባሮች ማከናወኛ ለሚወጣ ወጪ መሸፈኛ እንዲውል ለጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል ይህ ደብዳቤ ከደረስዎ ቀን ጀምሮ በ-- ----- ቀን ውስጥ እንዲያስረክቡ የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

"ከሰላምታ ጋር"

የኃላፊ ፊርማ

- የዕዳው መጠን ዕዳው እስከተሰላበት ጊዜ ብቻ ያለውን ዕዳ የሚያመለክት መሆኑ ይታወቅ፡፡

## የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋትና አስተዳደር
## የግልጽ ጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ

የጡረታ መዋጮ ከፋዩ ስም______________________________________________

የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ ዕዳ ብር____________________(________________________
______) ስላልከፈለ አድራሻው_______________ ከተማ _______________ ክፍለ ከተማ ______
______ ቀበሌ_______የቤት ቁጥር የሆነውን የጡረታ መዋጮ ባለዕዳውን ሀብቶች የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው አካል በአዋጅ ቁጥር 1268/2014 አንቀጽ 11እና አንቀጽ 12 ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በግልጽ ጨረታ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

1. የሀብቱ የጨረታ መነሻ ዋጋ ግምት ብር __________________ ነው፡፡
2. ስለሀብቱ አሻሻጥ መረጃ ከ_____________ክፍል ማግኘት ይቻላል፡፡
3. ተጫራቾች በቅድሚያ የጨረታ መነሻ ዋጋ 1/10ኛውን በጥሬ ገንዘብ ወይም ሲ.ፒ.ኦ ማስያዝ አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች ሀብቱን የሚገዙበትን ዋጋ በግልጽ በማስፈር በስም በታሸገ ኤንቬሎፕ አድርገው አድራሻው ------------------------------- በማለት አስፍረው እስከ -----------ቀን_____ዓ.ም. ከቀኑ___ ______ሰዓት ድረስ ቢሮ ቁጥር--------- በተዘጋጀው የግልጽ ጨረታ ሳጥን ማስገባት አለባቸው፡፡
5. ጨረታው _________ ቀን _______ ዓ.ም. ተዘግቶ በ _________ቀን በ_______ዓ.ም ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ---------- የስብሰባ አዳራሽ ይከፈታል፡፡
6. አሸናፊው ያስያዘው ገንዘብ ከግዥው ዋጋ ጋር ታስቦ ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ አሸናፊነቱ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ አጠናቆ በመከፈልና ሀብቱን መረከብ አለበት፡፡
7. የጨረታው አሸናፊ ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ 15 ቀናት ውስጥ አጠናቆ የማይከፍል ከሆነ ለጨረታው በዋስትና ያስያዘው ገንዘብ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሆኖ የጨረታው አሸናፊነቱ ይሰረዛል፡፡
8. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢው ስለሀብቶቹ አሻሻጥ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል ሊሰርዝ ይችላል፡፡